# RSV

**ሪስፓይራቶሪ ሲንሲሻል ቫይረስ (RSV) በጨቅላ ሕፃናት እና በእድሜ የገፉ አዋቂወች ላይ ከፍተኛ፣ ለ ሕይወት አስጊ ምልክቶችን የሚያስከትል የተለመደ የመተንፈሻ አካላት ቫይረስ ነው።**




**በከፍተኛ ሁኔታ ተጋላጭ የሆኑትን ለመርዳት የRSV ክትባቶች ለአዋቂዎች (50+)፣ ለጨቅላ ሕፃናት፣ እና ነፍሰጡር እናቶች ይሰጣል።**

## ማን አደጋ ላይ ነው?

- በተለይ ከ 6ወር በታች ያሉ ጨቅላ ሕፃናት
- ጊዜው ሳይሞላ የተወለዱ ሕፃናት
- አንዳንድ የመሰረታዊ የጤና ችግሮች ያለባቸው ህፃናትና አዋቂዎች
- አረጋዊያን
- በሽታ የመቋቋም አቅማቸው ደካማ የሆኑ ሰዎች
- በረጅም ጊዜ እንክብካቤ ተቋማት ውስጥ የሚኖሩ አዋቂዎች

## ምልክቶቹ ምንድን ናቸው?

- ትኩሳት
- ንፍጥ መፍሰስ
- አፍንጫ ማፈን
- ማሳል
- የጉሮሮ ህመም
- ሲር ሲር የሚል ትንፋሽ
- ራስ ምታት
- ድካም

## እንዴት ይሰራጫል?

RSV በሳል ወይም በማስነጠስ ጊዜ በሚወጡ የመተንፈሻ ፈሳሾች በቀላሉ ይተላለፋል፤ እንዲሁም ቫይረሱ ያለባቸውን በታዎች ነክተው ፊትዎን ሲነኩ ይተላለፋል።

**ለበለጠ መረጃ የQR ኮዱን ስካን ያድርጉ**

**ስለ ምልክቶች ጥያቄ ወይም ስጋት ካሎት በአቅራቢያዎ ያሉትን የጤና አገልግሎት ሰጪዎችን ያናግሩ።**

## የRSV ስርጭትን መግታት

- ብዙ ጊዜ የሚነኩ በታዎችን ያጽዱ
- በሽታው ካለባቸው ሰዎች ጋር ንክኪ አያድርጉ
- በህመም ጊዜ ቤት ይቆዩ
- የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ ያድርጉ
- እጆችዎን በተደጋጋሚ ይታጠቡ
- በሚያስሉበት እና በሚያስነጥሱበት ጊዜ አፎን ይሸፍኑ
- የሚችሉ ከሆነ ክትባት ይውሰዱ



Department of Public Health
CITY OF PHILADELPHIA

2026 ክረምት

*እርሶ (ወይም ልጅዎ) መተንፈስ ካስቸገራችሁ፣ በቂ ፈሳሽ ካልጠጠችሁ ወይም ምልክቶቹ ካልተሻሻሉ ወድያውኑ ወደ ድንገተኛ ህክምና ይሂዱ ወይም 911 ይደውሉ።*

**RSV በበልግ እና በክረምት ወቅት የበለጠ ይሰራጫል። በከፍተኛ የቫይረስ ኢንፌክሽን የመያዝ ከፍተኛ ስጋት ላይ ከመሆኑ ወይም በRSV ከፍተኛ ሁኔታ ሊታመሙ ከሚችሉ ሰዎች ጋር ከተገናኙ፣ ጤናማ ሆኖ ለመቆየት ተጨማሪ ጥንቃቄ ማድረግ አለብዎት።**

## አረጋውያን



RSV ክትባት ከባድ RSV ኢንፌክሽን እንዳይዝዎ ይጠብቅዎታል።

75 ዓመት እና ከዚያ በላይ ለሆናችው አረጋውያን አንድ መጠን ክትባት ይመከራል።

አንዳንድ 50 ዓመት እና ከዚያ በላይ የሆናችው አዋቂዎች የRSV ተገላጭነታቸው ከፍ ያለ ነው። ስለ ብቁነትዎ የጤና አገልግሎት ከሚሰጠዎት ጋር ይነጋገሩ።

## ነፍሰጡር የሆኑ ሰዎች



ነፍሰጡር የሆኑ ሰዎች በፅንሱ ላይ ከባድ RSV እንዳይከሰት መከተብ አለባቸው።

ለበለጠ መረጃ በአቅራቢዎ ካሉ የጤና አገልግሎት ሰጪዎች ጋር ይነጋገሩ።

## ጨቅላ ህፃናት



ከ8 ወር በታች ያሉ ጨቅላ ህፃናት ወላጅ እናታቸው በእርግዝና ወቅት RSV ክትባት ካልወሰዱ፣ በመጀመሪያው  RSV ወቅት የRSV አንቲቦዲ ማግኘት አለባቸው፡፡

## ሐኪሞን ሊጠይቁ የሚችሏቸው ጥያቄዎች

- ለከባድ RSV ተጋላጭ የሚያደርጉ የጤና እክሎች አሉብኝ?
- በዚህ ወቅት ስለ RSV እና ስለ ሌሎች የመተንፈሻ አካላት ቫይረሶች ማወቅ ያለብኝ አስፈላጊ ነገሮች ምንድናቸው?

Department of
Public Health
CITY OF PHILADELPHIA

የሕብረተሰብ ጤና ዝግጁነት ፕሮግራም | 215-683-0806

ስለ RSV ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት የመጀመሪያ ደረጃ የጤና አገልግሎት ከሚሰጥዎ የጤና ባለሞያ ጋር ይነጋገሩ